## ኣዎ ኣለ ነገር!!

ከዓሣዩ

ጀንበር በጠለቀ በነጋ በጠባ
ሁል ግዜ ግምገማ፤ሁል ግዜ ሥብሰባ፤
ሠራዊቱንና ነጭ ለባሹን ሲያምስ
እንደራበው ውሻ ቤቱን ሁሉ ሲያሥሥ፤
ኣለ ነገር እንጂ መለስን ያሥራደው
ክሥረቱን ሊሸፍን ዓረፋ እሥኪደፍቀው
ሌባ ጣት ቀሥሮ የሚያሥለፈልፈው ።
 ሺ ኮሎን ተባዝቶ ሥልጣን ቢይዝ መለስ
 ዜጋ እንደሁ እያዩ ዳር ድንበሩ ሲፈርሥ
 ግንባሩን ኣያጥፍም ካለመበት ሣይደርስ
 ቆርጦ ተነሣሥቷል እሱን ለመገርሰሥ ።
ኣዎ አለ ነገር!!
ዙሪያው ገደል ሁኖ ጭንቀት ሲያወራጨው
እሱ የደበቀንን እኛስ መቼ ኣጣነው ?

ታድያ

ዙርያውን ቃጠሎ እሣት ሲነድበት
ይበልጥ እንዲቃጠል ቤንዝን ነሥንሶበት
ማጋጋም ሲገባው ቆርጦ ለነጻነት፤
የፈራነው ደርሶ ቃልኪዳን ኣፍርሶ
ውኃ ቸልሶበት ግለቱን ቀንሶ፤
ነፍሥ ኣውጪኙን ሸሸ የፓርቲው ድሪቶ
ከመለስ ሊሸጎጥ ለሥልጣኑ ኣድልቶ ።
 እኮ ኣለ ነገር መሆኑ የማይቀር!!
 መለስ ምሥጢር ኣርጎት የደበቀን ነገር ፥
 ሥርዓቱ በሥብሶ ወድቆ ሲሰባበር
 በድርብ ድንጋይ ግንብ ዙሪያውን ቢታጠር
 እንደ እባብ ኣሣዶ ከገባበት መንደር
 ከተማሰው ጉድጓድ መወርወሩ ኣይቀር!!
 ኣዎ ኣለ ነገር! የተደገሰለት ፈጽሞ የማይቀር!!

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.